# ከኦሮምያ ክልል ኢሉ አባቦራ፣ በደሌ አማራዎች በአዲስ መልክ ማፈናቀል እንደቀጠለ ነው። ከመጋቢት 7 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከ3 ሺህ በላይ አማራዎች ተፈናቅለዋል

(ጌታቸው ሽፈራው)
ከኦሮምያ ክልል የአማራዎች መፈናቅል እንደቀጠለ ነው፡፡ አዲስ መፈናቀል ኢሉ አባቦራ፣ በደሌ ከመጋቢት 7/2010 ዓ.ም ጀምሮ ከአካባቢው **ከ3 ሺህ በላይ** ነዋሪዎች እንዲወጡ መደረጉን ተፈናቃዮቹ በስልክ ገልፀውልኛል።
ከኦሮምያ ክልል ኢሉ አባቦራ፣ በደሌ/77 ከሚባል ቦታ የተፈናቀሉት አማራዎች ወደ ባህርዳር መጥተዋል፡፡
~ ከኢሉ አባቦራ፣ በደሌ ተፈናቅለው ባህር ዳር የሚገኙት 64 አባውራዎች ሲሆኑ ቤተሰቦቻቸው ተበትነዋል!
~ ተፈናቃዮች ቤታቸው ተቃጥሎባቸዋል። ንብረታቸው ተወርሷል። ወድሟል።
~ የተገደለ፣ እጁን የተቆረጠ እና ቤቱ ውስጥ የተቃጠለም እንዳለ ተፈናቃዮቹ ገልፀዋል፡፡
~ ከአካባቢው የተፈናቃሉት በሺዎች የሚቆጠሩ ሲሆኑ የአካባቢው የኦሮምያ ክልልም ሆነ የየመንግስት አስተዳደር ምንም አይነት ጥበቃ ወይንም እገዛ አላደረገላቸውም። እንዲያውም እንዲፈናቀሉ እያደረገ ያለው የአካባቢው የመንግስት/ኦህዴድ መዋቅር እንደሆነ ገልፀዋል።
~ ከኢሉ አባቦራ፣ በደሌ የተፈናቀሉ አማራዎች ባህር ዳር የገቡት ዛሬ 13/2010 ዓም ሲሆን ብአዴን የባህርዳር ጎዳናዎች ላይም እንዳያድሩ በፖሊስ እያስነሳቸው ነው።
ከኦሮሚያ ክልል ኢሊባቡር አካባቢ ከተፈናቀሉት አማራዎች መካከል 64 ያህል በአሁኑ ወቅት ባህርዳር ክልል አስተዳደር ቢሮ እንደሚገኙ ታውቋል።
ከኦሮሚያ ኢሉ አባ ቦራ ተፈናቅለው ባህርዳር የገቡትን አማራዎች የክልሉ ፖሊስም ከተቀመጡበት እያስነሳቸው ነው።
የባህርዳር ሕዝብ እና ቤተ ክርስትያን መጠለያ ካልሆኗቸው የብአዴን ነገርም የታወቀ ነው።
የባህርዳር ሕዝብና ቤተ ክርስትያን ከለላ ካልሆኗቸው ብአዴን አዳኑን ወዳልታወቀ ቦታ እንደሚወስዳቸው ግልፅ ነው!
የባህር ዳር ሕዝብ ከቤንሻንጉል ለተፈናቀሉት እንዳደረገው አኩሪ ተግባር ከኦሮሚያ የተፈናቀሉትንም እገዛ እንደሚያደርግላቸው ይጠበቃል።

ከዚህ በታች በፎተዎች የሚታዮት ሰሞኑን ከኦሮምያ ክልል ኢሉ አባቦራ፣ በደሌ ተፈናቅለው ባህር ዳር የመጡ አማራዎች ናቸው



